# ዳር እስከ ዳር የሚገነፍል እና የማያቋርጥ ሕዝባዊ አመጽ ወያኔን ለማስወገድ አማራጭ የሌለው መፍትሄ — ይነበብ!!!

JUNE 1, 2015




አወ – የተግባር እርምጃ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ስለሆነ እኔ በበኩሌ ትግሌን በተግባር ጀምሬአለሁ፡፡ ከታች ለዘረዘርኳቸው እርምጃዎች እናንተም ጨምሩበትና ወደ ተግባር እንግባ!!!

«ጠብታ ውሃ ነው ደንጋይ የሚበሳ፣
እንጩህ ዝም ብለን – ሕዝብ እስከሚነቃ፣ አገር እስኪነሳ፡፡» – ሜሮን ጌትነት

እውነት ነው ሜሮን – እንጩህ !!! ዝምታው ይሰበር!!!

ህወሃት በሰላም፣ በምርጫ ስልጣኑን ይለቃል ማለት ሰማይ ይታረሳል ብሎ ማሰብ ማለት ነው፡፡ ይህን ጭራቅ ፀረ-ኢትዮጵያዊ የሽፍታ መንግሥት ለማስወገድ አማራጭ የሌለው መፍትሄ አንድ እና አንድ ነው – ዳር እስከ ዳር የሚገነፍል፣ ለእስር፣ ለእንግልት እና ለግድያ የማይበገር፣ ጠንካራ እና የማያቋርጥ ሕዝባዊ አመጽ ብቻ፡፡ ያለመስዋትነት ድል አይገኝም፡፡ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ አስረው፣ ሁሉንም ደብደበው፣ ሁሉንም ገድለው ስለማይጨርሱ፤ አንተ ሙተህልኝ እኔ ልኑር ከሚለው አስተሳሰብ በመላቀቅ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በጎሳ ሳንከፋፈል፣ ከዘላለም ባርነት የአንድን ቀን ነፃነት በማለም በያለንበት ሕዝባዊ አመጽ ማካሄድ ብቻ ነው ህወሃት/ ወያኔን ከስልጣኑ የሚያስወግደው፡፡

የወያኔ/ህወሃትን እኩይ ሴራዎች በማኅበራዊ ድህረ-ገጾች ማጋለጥ ከተጀመረ ወዲህ ይህ ነው የማይባል መነቃቃት በሕዝቡ፣ በተለይ በወጣቱ ዘንድ ሊፈጠር ችሏል፡፡ ከተለመደው የወያኔ/ህወሃትን እኩይ ሴራዎች በማኅበራዊ ድህረ-ገጾች ከማጋለጥ ባለፈ ትግላችንን ወደ ፊት አንድ እርምጃ ለማስኬድ ይረዳ ዘንድ እያንዳንዱ ዜጋ እጅግ ጠቃሚ የሚሆን የትግል ስልት ሊነድፍ ስለሚችል የበኩላችሁን እያጋራችሁን፣ እኔ ከዚህ በታች ለዘረዘርኳቸው እርምጃዎች እናንተም ጨምሩበትና ዛሬ ነገ ሳትሉ ትግላችሁን ወደተግባር መለወጥ ትጀምሩ ዘንድ ጥሪየን አቀርባለሁ፡፡

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በተለይም የጥቃት ግንባር ቀደም ሰለባ የሆንከው የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የጉራጌ፣ የሶማሌ፣ የጋምቤላ ልጅ፤ የኦርቶዶክስ እና የእስልምና ተከታይ ምንም ምርጫ የለህም – ትግልህን ከራስህና ከቤተሰብህ ጀምር !!!

ወገኔ ሆይ! እንግሊዞች የቀበሩትን የዘረኛነት መርዝ በሻዕቢያዎች በጥባጭነት፣ በአሜሪካኖች አይዞህ ባይነት፣ ስማቸው የቅዱሳን – ግብራቸው ግን የዳቢሎስ የሆኑት ህወሃቶች በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በጎጥ፣ በሃይማኖት እየከፋፈሉህ፣ አንድነትህ እና ሰላምህ ተናግቶ፣ እንዳትደራጅም ሆነህ ትገኛለህ፡፡ በተደራጁትም ውስጥ ወያኔ ሰርጎ በመግባት፣ ልዩነትን በመፍጠርና ምስጢራቸውን ለወያኔ አሳልፎ በመስጠት ሲያዳክሟቸው ኖረዋል፡፡ አሁንም ቀጥለዋል፡፡ "አውራው ሲጠፋ መንጋው ይበተናል" በሚለው ቀመር የተደራጁትንም ጠንካራ ተቃዋሚዎች፣ ለህዝብ ነፃነት ጥያቄ የሚያቀርቡትን እና የህዝባቸውን ብሶትና በደል የሚያጋልጡ ጋዜጠኞችህን፣ የሃይማኖት አባቶችህን የሃሰት ወንጀልና ምስክር በመፍጠር "አሸባሪ" የሚል ስም ሰጥቶ እያሰረ፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችህን ከትምህርታቸው እያባረረ፣ ትግላቸውን እያኮላሸ ቆይቷል፡፡ እያደረገም ነው፡፡ ኢንፎርሜሽን (መረጃ) እንዳትለዋወጥ እና ከወገንህ ጋር እንድነት መሥርተህ ሃይልና ጉልበት እንዳታገኝ እና ራስህን ነፃ አድርገህ እንዳትኖር ወያኔ አፍኖ እና አደንቁሮ እየከፋፈለህ፤ ደረጃ በደረጃ፣ ተራ በተራ እያንዳንድህን በተናጠል ለማጥፋት ሌት ከቀን ያለእንቅልፍ እየገዘገዘህ ይገኛል፡፡

ሕዝቡ የወያኔ/ሻዕቢያ ጥምር አገዛዝ መርሮታል፡፡ ሕዝቡ ምሬቱን አምቆ እንደያዘ እና በአገዛዙ እንደተማረረ እንኳንስ የወያኔ አባል ያልሆነው ቀርቶ አባላቶቻቸው ሁሉ ልባቸው እንደሸፈተ፤ ሆ ብሎ ለመነሳት ተነስ ብሎ የሚቀሰቅሰው ጠንካራ የተደራጀ ኃይል እና ተነስ የሚባልበትን ጊዜ እየጠበቀ እንደሆነ፣ ወያኔ ራሱ በሚገባ ያውቀዋል፡፡ ለዚህም ነው ያለምንም እረፍት እና መዘናጋት አንተ ተቸግረህ በምትከፍለው ግብር፣ በስምህ ተለምኖ በመጣው ብድርና እርዳታ፤ ስንት ሆስፒታል እና ክሊኒክ፣ ስንት ትምህርት ቤት፣ ስንት መንገድ፣ ስንት የመጠጥ ውሃ ሊገነባ የሚችለውን ገንዘብ፤ የሕዝቡን ልብ ሊያገኝበት ለማይችልበት ላልረባ ስብሰባ እያፈሰሰ፣ በተለይም ደግሞ በአሁኑ ወቅት አማራውንም ሆነ ኦሮሞውን እየገደለ እና እያደኸየ ያለው የሻዕቢያዎቹ ዲቃላ ህወሃት ሆኖ እያለ፤ በእንግሊዞች እና በሻዕቢያዎች በተደረሰው የዘረኛነት ድርሰት አማራን እና ኦሮሞን

የእደሜ ልክ ጠላት ለማድረግ፣ ሁለቱን ብሔሮች እርስ በእርስ በማጨፋጨፍ ትግሬዎቹ በብቸኝነት የአገሪቱን ሃብትና ንብረት ለመዝረፍ አሁንም አጠናክሮ መርዙን እየረጨ የሚገኘው፡፡

የተደራጀ እና ብቁ አመራር የሚሰጥ፣ ስለአንተ የሰብአዊ ሙብት መረገጥ እና ለተከፈተብህ የዘር ማጥፋት ዘመቻ የሚከላከል ጠንካራ ሃይል መጠበቅ መና ከሰማይ እንዲዘንብልን እንደመጠበቅ ማለት ነው፡፡ ሻዕቢያ እና ህወሃት የረጅም ጊዜ ዕቅዳቸው የትግራይ ትግሪኝ አገር መመሥረት፣ እስከዚያው በስልጣን ላይ እስካሉ ድረስ የአገሪቱን ሃብትና ንብረት መዝረፍ ነው፡፡

በሻዕቢያ እና በህወሃት መካከል ከማስመሰል ያለፈ ጥላቻ የለም፡፡ ህወሃቶች ለሻዕቢያ ሲታገሉ እንደኖሩት፣ የኢትዮጵያን ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ኤርትራን በማስገንጠል፣ የአሰብን ወደብ እና የባድሜን መሬት አሳልፈው እንደሰጡትና አሁንም እየሠሩ እንዳሉት፤ ሻዕቢያም በበኩሉ ጠንካራ የህወሃት ተቃዋሚ እንዲኖር አይፈልግም፡፡ ኤርትራ ውስጥ የነበሩትን የአነግን እና የአርበኞች ግንባርን ሠራዊት ያዳከመው ሻዕቢያ ነውና፡፡ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትም የኢትዮጵያ ሠራዊት የኢሳኢያስ አፈወርቂን መንግሥት እንዳይደመስስ የተደረገው በህወሃቶችና በመለስ ዜናዊ ቀጭን ትዕዛዝ ነው፡፡ አሁንም ዴምሃት የተባለ ለስሙ (ለሽፋን) የትግራይ ተቃዋሚ የሚባል፣ ነገር ግን ትግራይን እንደኤርትራ ለማስገንጠል በኢሳኢያስ አፈወርቂ አደራጅነት ተመሥርቶ ወደ **25000** የሚጠጋ ሠራዊት እንዳስመረቀ ሰምተናል፡፡ ሰሞኑን ከወያኔዎች የምንሰማው ዲስኩር ደግሞ የኤርትራን እና የኢትዮጵያን ሕዝቦች ግንኙነት ወደነበረበት ለመመለስ ጥረት ተጀምሯል ይላሉ – ድሮውንም ሕዝብ እየተላቀስ መለያየቱን ያመጡብን እና የጥላቻ መርዛቸውን የረጩብን ሁለቱ ህወሃቶች እና ሻዕቢያዎች ናቸው፡፡ ይህ የአሁኑ የሁለቱን ህዝቦች ግንኙነት ወደነበረበት ለመመለስ የሚባለው ማደናገሪያ፣ በማር የተለወሰ መርዝ በውስጡ እንደሚኖረው ከእስካሁኑ ተግባራቸው መገመት ይቻላል፡፡ ከእባብ እንቁላል እርግብ አይፈለፈልምና እነሱን ማመን በምንም፣ በፍጹም አይቻልም – ህወሃት እና ሻዕቢያን ማመን ቀብሮ ነውና!፡፡ ምክንያቱም ዴምሃት የተባለው አዲስ እና ሁለተኛ ዙር ተተኪ አስገንጣይ ድርጅት አሰብ የትግራይ ነው እያለ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ነው አላለም፡፡ አሰብ የወሎ ጠቅላይ ግዛት ክፍል የነበረ እንጅ የኤርትራም፣ የትግራይም ሆኖ አያውቅም፡፡ ይህ እንግዲህ ህወሃቶች ትግራይን እንደ ኤርትራ አስገነጠሉ እንዳይባሉ ከሻዕቢያዎች ጋር ያዘጋጁት ሴራ **(Plan-B)** መሆኑ ነው፡፡

የሻዕቢያዎቹ ውላጅ የሆነው የህወሃት አገዛዝ ኢትዮጵያውያንን በተለይም አማራዎች በነጻነት ተዘዋውረው እንዳይኖሩና እንዳይሠሩ፣ ከቤት ንብረታቸው እያፈናቀለ፣ ኦሮሞዎችን እያደነና ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታቸው እያፈናቀለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ያላቸው ትግሬዎች በመኖራቸው (እነኝህ ደግሞ ጊዜያዊ ጥቅማቸው ስለተከበረ ለጊዜው የህወሃት ደጋፊ ቢሆኑም ለዘለቄታው ከሻዕቢያ ጋር ላይተባበሩ ስለሚችሉ) ኤርትራውያኖችን ዩኒቨርስቲ አስገብተው እያስተማሩና እያስመረቁ ለፀረ-ኢትዮጵያውያን ህወሃቶች ጠንካራ አጋር እየፈጠሩ ይገኛሉ፡፡ ሱዳንም በበኩሏ ህወሃት ጠላቴ ያላቸውን አማራዎችን በማፈናቀልና መሬት አልባ በማድረግ፣ አፄ ዮሐንስ አንገታቸውን የሰጡለትን የአማራ ክልልን ሰፊ ለም መሬት በገጸ-በረከትነት ለሱዳን በመስጠቱ ከአማራ ክልል ተቆርሶ ለተሰጣት መሬት ወሮታ እና ዳርፉር ውስጥ በዜጎቹ ላይ በአደረሰው ጭፍጨፋ በጦር ወንጀለኛነት ተከስሶ በተገኘበት እንዲያዝ የተፈረደበትን የሱዳኑን ፕሬዚዳንት አሊ በሽርን መቀሌ ለጉብኝት በመጣበት ጊዜ እንዳይያዝ፣ ዳርፉር የተጨፈጨፉት ንጹሃን ዜጎች ደም ፍትህ እንዳያገኙ መለስ ዜናዊ አሊ በሽርን አስሾልኮ ከማስመለጡም በላይ የአፍሪካ ህብረትን በማስተባበር ፍርዱን እንዲያወግዙ በማስደረጉ፤ ህወሃት ከሱዳን ርካሽ ተወዳጅነትን እንዲያተርፍ አስችሎታል፡፡ ወያኔን ለመዋጋት የትጥቅ ትግል ጀምረው በአገሯ (በሱዳን) ውስጥ የሚዘዋወሩትን ታጋዮች ወያኔዎች እንደቤታቸው እየለቀሙ ለማሰር የሚያስችላቸውን ስምምነትም በቅርቡ ተፈራርመዋል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ሱዳን የወያኔን ተቃዋሚዎች እያደነች አሳልፋ ትሰጣለች ማለት ነው፡፡

ስለሆነም የትጥቅ ትግል የጀመሩ ተቃዋሚዎችን ነፃ መሬት እያሳጣቸው ነው፡፡ ህወሃትም በሰላም፣ በምርጫ ስልጣኑን ይለቃል ማለት ሰማይ ይታረሳል ብሎ ማሰብ ማለት ነው፡፡ ይህን ጭራቅ ፀረ-ኢትዮጵያዊ የሽፍታ መንግሥት ለማስወገድ አማራጭ የሌለው መፍትሄ አንድ እና አንድ ነው – ዳር እስከ ዳር የሚገነፍል፣ ለእስር፣ ለእንግልት እና ለግድያ የማይበገር፣ ጠንካራ እና የማያቋርጥ ሕዝባዊ አመጽ ብቻ፡፡ ያለመስዋትነት ድል አይገኝም፡፡ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ አስረው፣ ሁሉንም ደብደበው፣ ሁሉንም ገድለው ስለማይጨርሱ፤ አንተ ሙተህልኝ እኔ ልኑር ከሚለው አስተሳሰብ በመላቀቅ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በጎሳ ሳንከፋፈል፣ ከዘላለም ባርነት የአንድን ቀን ነፃነት በማለም በያለንበት ሕዝባዊ አመጽ ማካሄድ ብቻ ነው፡፡

ሁላችንም በያለንበት፣ በየምንሄድበት፣ ወዳጅ ዘመዶቻችን ባሉበት፣ በየማህበሩ፣ በየእድሩ፣ በየሥራ መስኩ፣ በየእምነት ተቋማቱ፣ በየትምህርት ቤቱ፣ በየመሥሪያ ቤቱ፣ በየጎዳናው፣ በየትራንስፖርቱ ወዘተ ሕዝቡ ፍርሃትን አስወግዶ ምሬቱን እያነሳ በይፋ ማውራት፣ መነጋገር፣ መንቃት እና ማንቃት፣ በሕቡዕ (በስውር) መደራጀት እና ማደራጀት፣ መታጠቅ እና ማስታጠቅ፣ መታገልና ማታገል ምንም አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው፡፡ ሥለሆነም እኔ በበኩሌ ከዚህ በታች የዘረዘርኳቸው ባለሁለት ምዕራፍ እርምጃዎች ትግላችንን አንድ እርምጃ ወደፊታ ያራምዳል ብየ አስባለሁ፡፡ እናንተም ጨምሩበት፡፡ እኔ ትግሌን ጀምሬአለሁ!!!

የትግል ምዕራፍ – አንድ

**1.** ትግል ከራስ ይጀምራል – ራስን ለትግል አዘጋጅቶ ሌላውንም ያለመሰላቸትና ያለተስፋ መቁረጥ ለትግል ማነሳሳት፡፡ የትግሉ መጀመሪያ እኔ ምን ለውጥ ላመጣ ነው**?** የሚለውን አስተሳሰብ መለወጥ፡፡ አንድ ሰው ዓለምን ሊለውጥ የሚያስችል እምቅ ችሎታ ሊኖረው ይችላል፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የታፈነ ሃይሉን ማውጣት ይጠበቅበታል፡፡ የተስፋ መቁረጥን እና የተሸናፊነትን ስሜት፣ እርስበርስ የመጠራጠርን እና የፍራቻን ስሜት መስበር አለበት፡፡ የጤፍ ቅንጣት ከጓደኞቿ ጋር ሆና የኩንታል ጆንያ ሞልታ ታቆማለች፡፡ እኔ ብቻየን እንዴት እሞላለሁ ብላ ብቻዋን ብትቀር፤ እንኳን የኩንታል ጆንያ ሚጢጢ ቢልቃጥ አትሞላም፡፡ ስለዚህ አንተ እና አንቺ ስትነሱ እናንተ ትሆናላችሁ፡፡ እኔ ስጨመር አኛ እንሆናለን፡፡ እኛ ከእነሱ ጋር ስንተባበር፤ የወያኔ ጥቃት ሰለባ የሆንነው አማራ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ ሶማሌ፣ ጋምቤላ፣ አንድ ሆነን ስንተባበር ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ኃያሎች እንሆናለን፡፡ ወያኔ በተለይ ቀበቶውን አጥብቆ እየሠራ ያለው አማራውን እና ኦሮሞውን በማጋጨትና በማጨፋጨፍ እድሜውን ማራዘም

ነው፡፡ በተለይም ደግሞ አማራ ኢትዮጵያሚነት ስሜቱን በቀላሉ ሊተው ባለመቻሉ ቀጥተኛ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ሰለባ ሆኖ ይገኛል፡፡ ስለሆነም አፍንጫን ሲመቱት ዓይን ያለቅሳል እና፣ ዛሬ በሌሎቹ ግለሰቦች በተናጠል ወይም በሌሎቹ ብሔሮች ላይ በጅምላ አደጋ ሲያደርስ ነገ በእኔም ሆነ በብሔሬ ላይ ተመሳሳይ ጉዳት እንዳይደርስ ብለህ አንተም ለወገንህ እንዳትከላከልለት እና አብረህ ብሶቱን ምሬቱን እንዳታሰማለት፣ ዛሬ አንተ ምንህ ተነካ? እያለ ለወገንህ እንዳትተባበር፤ ነገር ግን ተመሳሳይ ጉዳት ነገ በአንተ ላይ ሲደርስብህ ሌላው ወገንህ ለአንተም እንዳይደርስልህ እያደረገህ ነው፡፡ አንተም አብረህ እኔ ምን አገባኝ በማለት ለወያኔ ተባባሪ እና ጠንካራ ጉልበት እየሆንክው ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በተለይ አማራ ሕወሃት በ **1968** ሲመሠረት ጠላቴ ነው ብሎ በማኒፌስቶው ያስቀመጠው አማራውን ብቻ እንጂ ሌላውን አይደለም፡፡ ያንን የተነሳበትን ዓላማ ደረጃ በደረጃ እየፈፀመው በመሆኑ እና ወደፊትም ስለማያቆምልህ፤ በኋላ ጊዜው ረፍዶ ከእነ ዘርማንዝርህ ከመጥፋትህና ለእድሜ ልክ ባርነት ከመዳረግህ በፊት ራስህን አዘጋጅተህ ለአንተ እና ለልጆችህ ነፃነት የሚታገሉልህን ዓላማቸው ዓላማዬ፣ ብሶታቸው ብሶቴ፣ ጉዳታቸው ጉዳቴ ነው ብለህ ትግላቸውን ተቀላቀል፡፡

**2.** ጠንካራ የተደራጀ ሃይል ሳይጠብቁ – "ሁሉም አደራጅ – ሁሉም ተደራጅ፣ ሁሉም መሪ – ሁሉም ተመሪ" በመሆን ሁለግ ትግል ማካሄድ፡፡ ከላይ እንደገለጽኩት ጠንካራ ተቃዋሚ ሃይል እንዳታገኝ ህወሃት ወገቡን ታጥቆ ያለምንም መዘናጋት እየሠራ ነው፡፡ ስለሆነም "ሁሉም አደራጅ – ሁሉም ተደራጅ፣ ሁሉም መሪ – ሁሉም ተመሪ" በመሆን የትግሉን ሰንሰለት (ኔትውርክ) ማስፋፋት ግድ ይልሃል፡፡ ስለዚህ ተቀዳሚው ተግባር መንቃትና በሰፊው ማንቃት ነው፡፡ ሕዝቡ የንቃት ደረጃው ሲያድግ በቀላሉ ጠንካራ እምነትና መሠረት ይዞ ይደራጃል፡፡ ጠንካራ ድርጅት ሲፈጠር ለውጥ ያመጣል፡፡ ስለሆነም ሁሉም ትግሉን ከራሱ፣ ከቤተሰቡ፣ ከዘመዶቹ፣ ከጓደኞቹ መጀመር፣ ለጎረቤቶችህ ማሳወቅ፤ ለሃይማኖት አባቶችህ፣ የሃይማኖት አባቶችህ ለመንፈስ ልጆቻቸው፣ አስተማሪ ለተማሪው፣ ተማሪው ለወላጆቹ፣ በውጭ የምትኖሩ አገር ውስጥ ላሉ ዘመዶቻችሁ፣ በከተማ የምትኖሩ በገጠር እና በየክፍለሃገሩ ተበታትነው ያሉ ዘመዶቻችሁን፣ በየገጠር ቀበሌው ያላችሁ መምህራን፣ የግብርና እና የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በየቀበሌው ያለውን የቀበሌ አመራር፣ ታጣቂ ሚሊሻዎችና እና መላ አርሶአደሩን፣ በየቦታው የመዘዋወር ዕድል ያላችሁ በየሄዳችሁበት የምታገኙትን ወገናችሁን፤ ማስተማር፣ ማንቃትና ለትግል ማነሳሳት አለባችሁ፡፡ በተለይም የስነጥበብ ባለሙያዎች ከአድርባይነት ወጥተው በስነፅሁፍ፣ በግጥም፣ በዜማ ህዝቡን ለትግል ማነሳሳትና ወኔውን መቀስቀስ አለባቸው፡፡ በጋዜጠኛነት ሙያ የተሠማራችሁ በርካታ የቪዲዮ፣ የድምጽ፣ የፎቶግራፍ መረጃዎችን በቀላሉ የማግኘትና የመሥራት እድሉ ስላላችሁ የህወሃትን እኩይ ተግባር፣ በወገናችሁ ላይ የሚታየውን ችግር እና በደል ለህዝብ እና ለዓለም ማሳወቅ አለባችሁ፡፡

**3.** ኢንፎርሜሽን በሰፊው በመለዋወጥ ሕዝቡን በሰፊው ማንቃት፣ ለትግል ማነሳሳት እና ማደራጀት፡፡ ኢንተርኔት የምታገኙ ሁሉ የምታገኙትን የቪዲዮ፣ የድምጽ፣ የፅጽሁፍ፣ የስዕል መልዕክቶችን በኢሜይል፣ በብሉቱዝ፣ በሲዲ፣ በፍላሽ ዲስክ፣ በህትመት በማባዛት ኢንተርኔት እና የኢንፎርሜሽን ምንጭ ለሌላቸው በመሃል አገር እና በየክፍለሃገሩ ለሚገኙ ወገኖችህ ማዳረስ፡፡ ለደህንነታችሁ ሲባል በኮምፕዩተራችሁ ምንም ነገር ሴቭ አለማድረግ እና ወያኔ የበረሃ ስም እንደነበራቸው ሁሉ እናንተም ሌላ የብዕር ስም በመጠቀም በየመድረኩ እና በየቦታው የሚፈጸሙትን ግፍና በደሎችን በማህበራዊ ድህረ-ገጾች እና በምታገኙት የመገናኛ ዘዴ ማሳወቅ፣ ማጋለጥ፡፡ በማህበራዊ ድህረ-ገጾች አዘናጊ የሆኑ ቀልዶች፣ ፎቶዎች፣ ቪዲዮዎች የሚለጥፉትን ግሩፖች አለመቀላቀል ወይም **Un-friend** ወይም **Block** ማድረግ፡፡ የግሩፕ **Admin** የሆናችሁ የግሩፑ አባላት ግሩፓችሁን ለማስጠላት የብልግና እና አልባሌ ነገር የሚለጥፉትና ከግሩፑ ውጭ ማድረግ እንዲሁም አካውንታቸው እንዲዘጋ ለ **FB Admin** ሪፖርት ማድረግ፡፡ በየአጋጣሚው ለምታገኙት ወገናችሁ ሁሉ በአናንተና በወገናችሁ ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ በይፋ መነጋገር፡፡

**4.** በየአካባቢያችሁ ያሉ የተቃዋሚ ድርጅቶችን መደገፍና ማበረታታት፣ በሚጠሩት የሰላማዊ ሰልፎች እና የሕዝብ ስብሰባዎች በመገኘት ድጋፋችሁን መስጠት፣ ወያኔ ሊከፋፍላቸው ሲሞክርም ሆነ እነሱን ሲያዋክቧቸው ተስፋ ባለመቁረጥ ድርጊቱን በሞባይልም ሆነ በካሜራ በድምጽ፣ በፎቶ እና በቪዲዮ በመቅረጽ ማጋለጥ፡፡ በየቦታው ተደራጅታችሁ የምትታገሉ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች – ወያኔዎች በሌሊት እያሳፈኑ በተናጠል ጉዳት እንዳያደርሱባችሁ በአንድ ላይ በማደር ራሳችሁን መከላከል፡፡

**5.** ከወያኔ ጋር አለመተባበር፣ የእነሱን ትዕዛዝ እና ዕቅድ አለመፈፀም፣ ማበላሸት፣ ማጓተት፡፡ ወያኔ በሚጠራው ስብሰባ መቅረት፡፡ የተገኙም ቢቻል ምንም ነገር አለመናገር ካልሆነም የልባችሁን አለመናገር፡፡ እያንዳንዱን እርምጃችሁን በምስጢር ማከናወን፡፡ የሚሰጣችሁን ተግባር አለመፈፀም ወይም ማጓተት፡፡ ለሚለኩሱት የዘር እና የሃይማኖት ግጭቶች መሣሪያ አለመሆን (ከሌላ ጎሳ እና ሃይማኖት ጋር ሊያጋጩህ ሲሞክሩ የወያኔ ተንኮል መሆኑን አውቀህ ራስህን እየተከላከልክ ማሳለፍ)፣ ሌሎቹ ብሄሮች እና ሃይማኖችን በጥላቻ ቢያዩህ እንኳ ለወያኔ መሣሪ እንዳይሆኑ በትዕግስት ማስረዳት፣ ለሌላው ብሔር እና ሃይማኖት ያለህን አክብሮት በተግባር በማሳየት የወያኔን ተንኮል ማክሸፍ፡፡ ሁኔታው የተመቻቸለት በተቻለ መጠን የሌሎቹን ብሔሮች ቋንቋ ለመማርና ለማወቅ መጣር – ቋንቋ ትልቅ የግንኙነትና የአንድነት መሣሪያ ነውና፡፡

**6.** ወያኔን ሕዝባዊ መሠረት እና ድጋፍ ማሳጣት፡፡ የወያኔ መንግሥት ያለመሠረት (ያለ ሕዝብ ፍቅር) በጥግንግን ድጋፍ (በጦር ኃይል፣ በሆድ አደር ደህንነቶች እና ካድሬዎች ጨኸት ብቻ) የቆመ፣ በደንጋይ ላይ ደንጋይ ተረብርቦ እንደቆመ ፎቅ ማለት ነው፡፡ ሕዝባዊ ፍቅር ስለሌለው ያለ ደጋፊዎቹ ራሱን ችሎ መቆም አይችልም፡፡ እድሜ እና ጉልበት የሰጠነው እኛ ራሳችንን የህሊና እስረኞች በማድረጋችን፣ በእኛ ዝምታ እና እኔ ምን አገባኝ በሚል ተባብሮ በአለመታገል ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ወያኔን ለመጣል ድጋፉን ማሳጣት ግድ ይላል፡፡ አሜሪካ የሶቪየትህብረትን አፈራርሳ ስትጥል መጀመሪያ አጋር አገሮቿን ምሥራቅ አውሮፓን እና ሶሻሊዝምን እንከተላለን ያሉ ታዳጊ አገሮችን – ኢትዮጵያን ጨምሮ በማዳከምና በማስከዳት ነበር፡፡ አሁንም ወያኔ ብቻውን ራሱን ችሎ ስለማይቆም፣ የተሸከመው ወንጀል ራሱን ገፍትሮ ስለሚጥለው በተባበረ የህዝብ ክንድ ተፈንግሎ ይወድቃል፡፡ ጥርስንም ለማውለቅ መጀመሪያ ማነቃነቅ እንደሚያስፈልግ ሁሉ ወያኔን ነቅሎ ለመጣል፣ ተደግፎ የቆመበትን ሠራዊቱን፣ ደህንነቱን እና ካድሬዎቹን በያለንበት መቦርቦር እና የሚያደርጉትን ድጋፍ በማላላት፣ ሕዝባዊ መሠረት እንዲያጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ በውትድርና፣ በፖሊስነት፣ በሚሊሺያነት ወዘተ የሚያገለግሉ ልጆቻችሁን እና ወንድሞቻችሁን እንዲሁም የወያኔ ፕሮፖጋንዳ እውነት መስሏቸው

ከልባቸው ደፋ ቀና የሚሉትንም ሆነ የወያኔን ሴራ እያወቁ ሆድ አደር የወያኔ አገልጋይ ባሪያ ካድሬ (ባንዳ) ዘመድ ያላችሁ ሁሉ፤ ከወያኔ ጋር እንዳይተባበሩ መምከር እና የህወሃት/ሻዕቢያን የረቀቀ ምስጢር፣ ፀረ-ኢትዮጵያዊነታቸውን፣ ፀረ-አማራነታቸውን፣ ፀረ-ኦሮሞነታቸውን፣ ፀረ-ጉራጌነታቸውን፣ ፀረ-ሶማሌነታቸውን እና ፀረ-ጋምቤላነታቸውን በፈፀሟቸው እና እየፈፀሟቸው ያሉትን የዘር ማጥፋት ወንጀሎች በማሳወቅ እውነቱን እንዲረዱ ማድረግ፡፡ ሌላው ብሔር በተወላጆቹ ሲመራ አማራ ግን ብአዴን በተባለው አማራን በጠላትነት ፈርጆ አማራን ለማጥፋት በታገሉና አሁንም እየታገሉ ባሉ የሻዕቢያዎች እና የህወሃቶች ስብስብ እየተመራ እና ለጥፋት እየተጋለጠ ያለ በመሆኑ፤ ብአዴን አማራውን እንደማይወክል በማሳወቅ፤ በባንዳነት እያገለገሉት ያሉትን ሆድ አደር ካድሬዎች እና ደህንነቶችን በጓደኞቻቸው፣ በዘመዶቻቸው፣ በሃይማኖት አባቶቻቸው አማካኝነት የወገናቸውና የራሳቸው ጠላት ለሆነው ህወሃት ተባባሪ እንዳይሆኑ፤ ሌላ የሥራ አማራጭ እየፈለጉ እንዲለቁ፣ ካልሆነም የወያኔ የብረት ክንድ ሆነው በህዝባቸው ላይ በደል እንዳይፈጽሙ እና እርምጃ እንዳይወስዱ ማስደረግ፣ እምቢ ብሎ ከወያኔ ጋር የሚተባበረውን ማውገዝ፣ ማሰወገዝና ከማህበራዊ ኑሮ መነጠል፡፡

**7.** ወያኔዎችን እና ሆድ አደር ካድሬዎችን ማግለል፡፡ ከወያኔ፣ ከደጋፊ ትግሬዎቸ፣ ካድሬዎች እና ታማኝ ባንዳ ጀሌዎቻቸው ጋር ምንም ዓይነት ኢኮኖሚያዊም ሆነ ማህበራዊ ግንኙነት አለማድረግ፣ ከአንተ በሚያግበሰብሱት ገንዘብ አንተኑ እየገደሉበት ስለሚገኙ ከንግድ ተቋማቸው ምንም ነገር አለመግዛት፡፡ ለዚህ ደግሞ የህወሃት ካምፓኒዎችን፣ የትግሬዎችን እና የካድሬዎቻቸውን የንግድ ተቋማትን እየለዩ ለህዝብ፣ ለቤተሰባችሁ፣ ለጓደኞቻችሁ ማሳወቅ፡፡

**8.** የራሳችሁን እና የወገናችሁን ጤንነት መጠበቅ፣ የጤና ኤክስቴንሽኖችን ብሊድ ቁጥጥርን በሚመለከት አለመተባበር እና ከትግሬ ሃኪሞች አለመታከም፡፡ የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚፈጽሙበት አንዱ ስልት በህክምና ነው፡፡ ከበሽታችሁ ጋር የማይገናኝ መድሃኒት ወይም ጊዜው ያለፈበት፣ ወይም ከሚያስፈልጋችሁ መጠን በላይ እና በታች በማዘዝ፣ በክትባት ስም የኤችአይቪ ቫይረስ የተበከለ መድሃኒት በመከተብ፣ የማምከኛ መርፌ በመውጋት፣ ወዘተ ስለሆነ በትግሬ ሃኪሞች አለመታከም፤ ከአዲግራት መድሃኒት ፋብሪካ የተዘጋጁ መድሃኒቶችን አለመጠቀም፡፡ ጠንክረህ ልትታገልና ታግለህ ማሸነፍ የምትችለው ጤንነትህን ስትጠብቅ ነውና፤ በተለይም ከተከፈተብህ የኤችአይቪ ማስፋፊያ ዘመቻ ራስህን በመጠበቅ ጤናማና ጠንካራ ዜጋ መሆን ይጠበቅብሃል፡፡ በነጮቹ እርዳታ በሚታገዙት በዲኬቲ-ኢትዮጵያ፣ በብሉስታር፣ በማሪስቶፕስ ክሊኒክ ውርጃን በመፈፀም፣ እንዲሁም በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አማካይነት ቤት ለቤት በሚሰጥ ጥብቅ የወሊድ ቁጥጥር ስለሆነ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ለወገናቸው የዘር መጥፋት መሣሪያ መሆናቸውን እንዲያቆሙ ማንቃት፡፡ መለስ ዜናዊ በአንድወቅት ትግራይ የወሊድ ቁጥጥር አጠቃቀም ላልቷል ተብሎ ሲጠየቅ – ተውት ይወለድ፡፡ ቁጥራችን ይጨምራል፡፡ የሚበላ ሆድ ብቻ ይዞ አይወለድም፡፡ የሚያስብ ጭንቅላት፣ የሚሠራ እጅ ይዞ ነው የሚወለደው ነው ያለው፡፡ ሌላው ብሔር በተለይ አማራው ጠላት ስለሆነ ነው እንዳይወልድ የማምከኛና የማኮላሻ ዘመቻ የተከፈተበት፡፡

**9.** በምርጫ አለመሳተፍ – ጭራሹንም አለመመዝገብ፡፡ ምርጫን በሚመለከት አስመራጮቹ (የምርጫ ቦርዶቹ) እነሱ፡፡ ድምጽ ቆጣሪዎቹ እነሱ፡፡ ታዛቢዎቹ እነሱ፡፡ ምንጊዜም በየምርጫ ጣቢያው ለምርጫ በተመዘገበው ሰው ብዛት ልክ ተለዋጭ የድምጽ መስጫ ወረቀት ተዘጋጅቶ ስለሚቀርብ፤ መረጣችሁም አልመረጣችሁም ወያኔ ምርጫ አደረገ ከማስባል ባለፈ ምንም ውጤት የለውም፡፡ ስለሆነም ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ እስካልተቋቋመ፣ ከሚሊሻዎች እና ከካድሬ ወከባ ነፃ የሆነ ምርጫ እስካልተደረገ ድረስ ማንም ሰው ለምርጫ እንዳይመዘገብ ማድረግና ማስደረግ፡፡ ለምርጫ ባለመመዝገባችሁ ወያኔ የሚያደርስባችሁን የተለያየ ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ጫና ተጋግዞ ለመረዳዳትና ችግሩን ለመቅረፍ መሞከር፡፡

**10.** የሌላውን ሃይማኖት ማክበርና የራስህን ሃይማኖት አጠንክሮ መያዝ፣ መጠበቅ፡፡ የኦርቶዶክስ እና የእስልምና ሃይማኖቶችህን ለማጥፋት እርስ በእርስ እንድትጋጭ፣ የእምነት ተቋማትህ፣ የሃይማኖት መሪዎችህ ተደፍረዋል፡፡ ሃይማኖትህን ለማጥፋትም ወያኔ ደፋ ቀና እያለ ይገኛል፡፡ የወያኔ መንግሥት እስኪወድቅ ድረስ ሁሉም በየእምነቱ ያለማቋረጥ ጸሎት እንዲያደርግ ለሃይማኖት አባቶችህ ማሳሰብ፡፡

**11.** ቅርስህን፣ ታሪክህን እና ባህልህን መጠበቅ፡፡

ወያኔዎች ታሪክ አጥፍተው ታሪክ እንሠራለን ይላሉ፡፡ እርግጥ ነው የኢትዮጵያን እና የጀግኖች አባቶቻችንን ወርቃማ ታሪክ ጥላሸት እየቀቡ፣ የኢትዮጵያ እውነተኛ ታሪክ እንዲጠፋ መረጃ እና ቅርሶችን በማስወደም እና በዘረፋ በስፋት ተሠማርተዋል፡፡ የራሱን ታሪክ እና ማንነቱን ጠንቅቆ ለማያውቀው ግልብ ትውልድም የእንጀራ አባቶቻቸው ጣሊያን እና ሻዕቢያ በደረሱላቸው የተጣመመ ታሪክ ጭንቅላታቸውን እየሞሏቸው አዲሲቷን ኢትዮጵያ እንመሠርታለን እያሉ ይገኛሉ -ጠላቶቿ ያላሉትን የእናት ጡት ነካሽ ጭራቅ የእንግዴ ልጆቿ (ህወሃትና ሻዕቢያ) ግን የኢትዮጵያን ታሪክ የ 100 ዓመት ታሪክ ነው ሲሉን መክረማቸውንም አንዘነጋውም፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ከእነ ማሥረጃው እና ጥልቅ እውቀቱ ጋር የሚገኘው በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በመሆኑም፣ ኦርቶዶክስም አንድነትን፣ ሰላምን፣ ፍቅርን ስለምትሰብክና ስለምታስተምር የቤተክርስቲያንን አስተዳደር በትግሬ ታጋይ ካህናትና በተሃድሶ ካድሬ ሊቃውንት በመተካት፣ ሙስና እና ዘረኝነት በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ እንዲስፋፋ በማድረግ፣ የቤተክርስቲያንንም ቅርስ በማስዘረፍ እና ገዳማትን ሳይቀር በማቃጠል ዮዲት ጉዲት ካደረሰችው ጥፋት ያልተናነሰ ውድመት እየደረሰ ይገኛል፡፡

ወያኔ ትውልዱን የሚገድልበት ሌላው ስትራቴጂ ደግሞ ወጣቱን “አደገኛ ቦዘኔ” ተብሎ በመፈረጅ፤ በመለስ ዜናዊ ታውጆ እስከአሁን ድረስ በይፋ ባልተሰረዘው በደህንነቶች ትዕዛዝ ማንናኛውም ፖሊስ ወይም ታጣቂ ነፃ እርምጃ የመውሰድ (ያለፍርድ የመግደል) ስልጣን የዜጎችን ሕይወት በማጥፋት ብቻ አይደለም፡፡ የወጣቱን ስነልቡና በማላሸቅና ወኔ በመስለብ፣ ከኢትጵያዊነት ስነ-ምግባር ውጭ ባህላችንን በመበረዝና ግብረ-ሰዶማዊነትን በማስፋፋት፣ “መስረቅም ሥራ ነው – እስካልተያዙ ድረስ” ብሎ በይፋ በማወጅ መላ አገሪቱን በሙስና በመዝፈቅ፤ ለአገሩና ለወገኑ ደንታቢስ የሆነ፣ ራስ ወዳድና ለዘረፋ የሚተጋ ትውልድ በማፍራት ጭምር ነው፡፡ ስለሆነም ሕዝቡ በየእምነት ተቋማቱ የሚገኙ ታሪካዊና

ሃይማኖታዊ ቅርሶችን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ወጣቱም ታሪኩን እና ማንነቱን ጠንቅቆ ያውቅ ዘንድ፣ ሕዝብ እስኪሰለች ድረስ በውሸት ማደናቆር በለመደው በወያኔ ልፈፋ ብቻ አምኖ ያንኑ ውሸት እውነት አድርጎ መቀበል ሳይሆን፣ እውነቱ ምንድን ነው? ከኢትዮጵያ ጠላትነት ውጭ በገለልተኛነት ያሉ አካላት ምን ይላሉ? ብሎ በመጠየቅና በማንበብ ማመዛዘን አለበት፡፡ ወያኔ – ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል በሚለው ፍልስፍና ውሸታቸውን እስኪያስታውከን ድረስ ይጮኩብናል፡፡ እኛ ደግሞ እውነት ተዳፍና እንዳትቀር ያለምንም መሰላቸት እና መሸማቀቅ ከተቀበረበት ማውጣት ይኖርብናል፡፡ ለዚህ ደግሞ የተማረው ክፍል በተለይም የታሪክ እና የህግ ምሁራን ወያኔ ለሚያደርገው እና ለሚናገረው ሁሉ አጸፋ የመስጠትና ሕዝቡን ከመደናገር እና ከስህተት የማዳን አገራዊ እና ሞራላዊ አለባቸው፡፡ ወጣቱ ትውልድ በጫትና በተለያየ ሱስ ራሱን ባለመጥመድ፣ የራሱን ዕንቁ የሆነ ባህልና ወግ በድንቁርና ሳይንቅና ሳያንቋሽሽ ጠብቆ ማቆየት፤ የምዕራባውያንን ርካሽና ቆሻሻ በህል ሳይሆን፣ ጠቃሚውን፣ የሥራ ትጋታቸውን፣ የምርምር ክህሎታቸውን፣ ወዘተ መቅሰም ይኖርበታል፡፡ ወያኔ አንተን ለማዘናጋት በየመገናኛ ብዙሃኑ ረጅም የጊዜ ሽፋን ሰጥቶ እና ከፍተኛ ወጭ አውጥቶ የሚያራግበው የእግር ኳስ ዝና እና ሃተታ ለአንተ የህይወትህን ጎደሎ አንድ ሳንቲም አይሞላልህም፡፡ ልፈፋ ጊዜህን፣ ገንዘብህን፣ አዕምሮህን ማባከን የለብህም፡፡ ለአንተ ለወደፊት ማንነትህ የሚጠቅምህ እና አንተም ለአገርህና ለወገንህ የምትጠቅመው የአውሮፓን እግር ኳስ በማድነቅ እና የተጫዋቾችና ታሪክ በመሸምደድ ሳይሆን፤ የአንተ እና የኑሮህ መሻሻል በመሆኑ ስለራስህ እና ስለአገርህ ብታስብ ነው የሚጠቅምህ፡፡ ስለሆነም ስሜት ስለሆነ ነው በሚለው የማታለያ ቃል ማንነትህን ማጣት የለብህም፡፡

የትግል ምዕራፍ – ሁለት

ትግሉ እየጠነከረ ሲሄድ ተጨማሪ አስገዳጅ እርምጃዎችን መውሰድ፡

**12.** ግብር እና ሌሎች መዋጮዎችን አለመክፈል፣

**13.** ልጆቹን ትምህርት ቤት አለመላክ፣

**14.** የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ፣

**15.** ወደየ ወረዳው ለሥራ የሚመጡትን የበላይ አካላት አለማስተናገድ፣

**16.** ወዘተ … ጨምሩበት!!! “ሁሉም አደራጅ – ሁሉም ተደራጅ፣ ሁሉም መሪ – ሁሉም ተመሪ” መሆን አለብን!!!!!!

ንቃ !!! ተደራጅ!!! ታጠቅ!!! ተነስ!!! ታገል!!!

አንድነት ኃይል ነው – ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ይባላልና

ያለመስዋዕትነት ድል የለም!!!

ከዘላለም ነፃነት – የአንድ ቀን ነፃነት!!!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!!!

መይሳው ተውድሮስ